# ADDA BILISUMMAA OROMOO

**OROMO LIBERATION FRONT**

**جبهة تحرير اورومو**

Gaafa: 15/04/2016 تاريخ
Date:

Lakk.: 007/stm/abo/2016 رقم
No.:

**በወያኔ የደህንነት ሃይል ትዕዛዝ የ'ኦህዴድ' 'ጨፌ ኦሮሚያ' የሚያወጣው ማንኛውም ኣዋጅ የኦሮሞን ህዝብ ሊወክል ኣይችልም**

*(ከኦነግ የተሰጠ መግለጫ)*

'ጨፌ ኦሮሚያ' የተባለው የ'ኦህዴድ' ምክር ቤት በወርሃ ታህሳስ 2015ዓም ያወጣውን የኦሮሚያ ከተሞች ኣዋጅ ተብዬ ባለፈው ሳምንት ተካሄደ በተባለው መደበኛ ስብሰባ በድጋሚ መልሰን በማየት ኣንዳንድ ነጥቦችን ኣስተካክለን ከፊሉን ደግሞ ሰርዘናል በሚል ኣስታውቋል። ይሁን እንጂ በኦሮሚያ ላይ የተዘረጋው ይህ የወያኔ ደህንነት ቅርንጫፍ የሆነ ድርጅት፡ በኦሮሞና በኦሮሚያ ጉዳይ ላይ ህግም ሆነ ማንኛውንም ኣዋጅ ለማውጣት ኣንዳች መብትም ሆነ ህዝባዊ ውክልና የለውም።

'ኦህዴድ' የሕወሃት ተላላኪና በትግራይ ዋሻ ውስጥ ኣዴት በተባለ ቦታ ከደርግ ሰራዊት ምርኮኞች በወያኔ የተጠፈጠፈ ድርጅት መሆኑን የኦሮሞ ህዝብ በሚገባ ያውቃል። ይህ የወያኔ ተላላኪዎች መዋቅር በኦሮሞ ህዝብ ዘንድ ኣንድ ጊዜም ተቀባይነትን ኣግኝቶ ኣያውቅም። የተመሰረተበት ዓላማ በኦሮሚያ ውስጥ የወያኔ ተወካይ ወይንም ቅጥረኛ ሆኖ የሕወሃትን ጥቅም ማስጠበቅ እንጂ የኦሮሚያን ፍላጎትና ጥቅም ማስጠበቅ ኣይደለም። ይህ የጠላት ተላላኪዎች ስብስብ የሆነው ድርጅት ለኦሮሞ ህዝብ ያልሰራውን ሰርቻለሁ ብሎ ዘወትር ውሸት ከማራገብ በስተቀር ለኦሮሞ ህዝብ ፍላጎትና ጥቅም ኣንዴም ቆሞ ኣያውቅም። የኦሮሞን ህዝብ ድምጽ ኣሰምቶ ኣያውቅም። ለዚህ ስላልተመሰረተም ስለህዝቡ መብትና ፍላጎት ሊናገር ኣይችልም።

በኦፒዲኦ ውስጥ የሚገኙ በሺዎች የሚቆጠሩ ብሄርተኞች ይህንን ሁኔታ ለማሻሻል ብዙ ቢደክሙም ለራሳቸውም የወያኔ ጥቃት ሰለባ በመሆን ኑሮኣቸው ኣደጋ ላይ ቀድቆ ጥረታቸው በከንቱ ሜዳ ላይ ቀረ። ይህንን ተላላኪ ድርጅት ከእኩይ ዓላማው መልሶ ለኦሮሞ ህዝብ ጥቅም እንዲውል ለማድረግ ካሁን በኋላ ኣንዳች ተስፋ እንደሌለው በኦፒዲኦ ውስጥ ያሉ ብሄርተኞች ይህንን እውነታ በሚገባ ኣረጋግጠዋል። ይህ ኦህዴድ የተባለው ቡድን ወያኔ የኦሮሞን ህዝብ በኣገዛዙ ስር ለማስገበት ሊቆጣጠርበት የሰራው የሕወሃት የስለላ መረብና የፖለቲካ መሳሪያ ነው። በኣጭሩ ኦህዴድ ወያኔ የኦሮሞን ህዝብ የሚደበድብበት፣ የሚገድልበትና የሚያሰቃይበት የሕወሃት ቡድን በትር ነው። ጨቋኙ የባዕዳን ስርዓት ላለፉት 25 ዓመታት የኦሮሚያን የተፈጥሮ ሃብት ሲመጥጥበት የነበረና ኣሁንም እየመጠጠበት ያለ የወያኔ መሳሪያ ነው። ባዕድ ጨቋኝ ስርዓት ተጠቅሞበት የኦሮሞን ህዝብ ከመሬቱ ያፈናቀለና እያፈናቀለ ያለ መሳሪያ ነው። ወያኔዎች ኦፒዲኦንና 'ጨፌ ኦሮሚያ' የተባለውን በኦፒዲኦ የተሞላውም ምክር ቤት በመጠቀም በኦሮሚያ የገጠርና ከተማ መሬት ላይ ፈላጭ-ቆራጭ ሆኑ።

ስለሆነም ኦፒዲኦ በኦሮሞ ስም የኦሮሞን ህዝብ ፍላጎትና ጥቅም ኣሳልፎ ለጠላት የሰጠ፣ ለኦሮሞ ህዝብ ወገንተኝነቱ ያላሳየ፣ የኦሮሞ ብሄራዊ ስሜ በውስጡ እንዳይጎለብትና እንዲላሸቅ ያደረገ፣ የወያኔን ትዕዛዝ ስራ ላይ ለማዋል እንጂ እራሱ ኣንዳች ስልጣንና ሃላፊነት የሌለው፣ ሃላፊነትም የማይሰማው፣ ኦሮሞና ኦሮሚያን እያደማ ያለ ቡድን ነው።

የኦፒዲኦ ምክር ቤት፥ 'ጨፌ ኦሮሚያ'፥ የኦሮሞ ሃገር ኣስተዳደር  የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሳይሆን፡ የሕወሃት ቡድን በኦሮሚያ ውስጥ እየፈጸመ ያለውን የፖለቲካ ጭቆናና የኢኮኖሚ ዝርፊያ ህጋዊ ለማስመሰል ያለኣንዳች ፍትሃዊና ነጻ ምርጫ በሃይል በኦሮሞ ህዝብ ላይ የሾመው የቅኝ ኣገዛዝ ስርዓት መዋቅር ነው። የኦሮሞ ህዝብ በኢትዮጵያ "ፌዴራል" መንግስትም ሆነ በኦሮሚያ ኣስተዳደር ውስጥ ተወካይ የለውም። በፌዴራሉ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ውስጥም ወኪል ወይንም ድምጽ የለውም።

ስለሆነም የወያኔ ስርዓት ፌዴራል መንግስትና ተቀጽላው የሆነው "ጬፌ ኦሮሚያ" የሚያስተላልፈው ማንኛውም ውሳኔ በኦሮሞ ህዝብ ዘንድ ተቀባይነት የለውም። "የጨፌ ኦሮሚያ" ምክር ቤት የኦሮሞን ህዝብ ሊወክል የማይችል የወንጀለኞች ስብስብና የሕወሃትን ጥቅም ለማስጠበቅ ብቻ በኦሮሚያ ውስጥ ላለፉት 25 ዓመታት ሲፈስስ ለነበረውና ኣሁንም እየጎረፈ ላለው ደም ተጠያቂ የሆነ ቡድን ነው።

የወያኔ ስርዓትና ቅጥረኛ ተላላኪዎቹ ከኦሮሞ ህዝብ በገጠማቸው ብርቱ ተቃውሞ የሚይዙትንና የሚጨብጡትን በማጣት ውጥረት ውስጥ ገብተው እየዋተቱ እንዳለ ከስርዓቱ ሚዲያና መገናኛ ብሁሃን በተደጋጋሚ ይሰማል።

በህዝባዊ ትግል የስርዓታቸው ፍጻሜ ሲቃረብ ጊዜ ለመሸመት ብለው ኣንዳችም እውነታ የሌለው ውሸት ኣዋጅ ለይስሙላ ለውጥና ማታለያ እያወጁ ይገኛሉ። በዚህ ኣዋጅ ኣሳብበው ጊዜ ለማግኘትና የህዝቡን እንቅስቃሴ ለማርገብ "የፊንፊኔን ማስተር ፕላን ህዝቡ ስለተቃወመ ትተነዋል" ብለው ካሁን በፊት እንዳላወጁ ኣሁን በሌላ መልኩ እኩይ እቅዱን ስራ ላይ ለማዋል ከንቱ ጥረት ተታይዘዋል። በፊንፊኔ ኣካባቢ ለሚገኙ ኣርሶ ኣደሮች የተሻለ ካሳ ሰጥተናቸው እነሱ የሚንኖሩበትን መሬት ለኢንቨስተሮች እናድላለን በሚል ትተነዋል ያሉትን የፊንፊኔ ማስተር ፕላን ውስጥ ለውስጥ ስራ ላይ እያዋሉ ነው።

የኦፒዲኦ "ጨፌ ኦሮሚያ" ኣሻሽለነዋል በማለት ያወጣው ኣዋጅም በርካታ ያልተስተካከሉና ግልጽ ያልሆኑ ጉዳዮች ኣሉት። የኦሮሞን ህዝብ ለመዋሸትና ለማታለል ኣሻሽለናል ኣሉ እንጂ ከመሰረቱ የተቀየረ ኣንዳች ነገር የለም። የኦሮሞ ህዝብ በግልጽ የሚያውቀው እውነታ በ"ጨፌ" ይሁን በኦፒዲኦ ኣልያም በማንም ስም የሚወጣ ማንኛውም ኣዋጅ በኦሮሞ ህዝብ ዘንድ ተቀባይነት ኣይኖረውም።

ያም ሆነ ይህ የኦሮሞ ህዝብ እያቀረበ ያለው የመሬትና የኦሮሚያ ከተሞች ኣስተዳደር ጥያቄ የፖለቲካ ጥያቄ ነው። በኦሮሚያ ውስጥ የሚገኙ በርካታ ከተሞች የቅኝ ገዢ ስርዓት የጦር ሰፈር፥ በሃበሻ ቋንቋ ከተማ(Military garrisons) የተባሉ መሆናቸው በገሃድ ይታወቃል። ስለሆነም ባዕዳን ሰፋሪዎች በሃይል በኦሮሞ ህዝብ መሬት ላይ ሰፈር በመሰረቱበትና በተደራጁበት ሁኔታ ውስጥ የኦሮሞን ህዝብ የማይወክል ኣንድ ኣካል ከባዕድ ጨቋኝ ስርዓት በተሰጠው ፖሊሲና መመሪያ የሚያወጣ ማናቸውም ኣይነት የኦሮሚያ ከተሞች ኣዋጅ ተቀባይነው የለውም። ስራ ላይ ለማዋል በሂደት ላይ ያለው የኦሮሚያ ከተሞች ኣስተዳደር ህግና ኣዋጅ የቅኝ ገዢ ስርዓትን ፖሊሲና እስትራቴጂ በመተግበር የሕወሃትን ጥቅም ለማስጠበቅ የታቀደ ነው።

በመጨረሻም የኦሮሞ ህዝብ ተቃውሞ የፊንፊኔ ማስተር ፕላን ኣልያም የኦሮሚያ ከተሞች ኣዋጅ ተቃውሞ ብቻ ሳይሆን የወያኔ ኣምባገነን ስርዓት በኦሮሞ ህዝብ ላይ የዘረጋውን የባዕዳን የጭቆና ስርዓት ከላዩ ላይ ኣሽቀንጥሮ ለመጣል የሚካሄድ ትግል ነው። የኦሮሞ ህዝብ ጥያቄ ሁሉን ኣቀፍ የሃገር ባለቤትነት መብት ጥያቄ ነው፥ የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት ጥያቄ ነው።

የኦሮሞ ህዝብ የተነፈገውን የፖለቲካና የኢኮኖሚ መብቱን ሙሉ በሙሉ ከእጁ ኣስገብቶ በሃገሩ ላይ በዲሞክራሲያዊ ስርዓት እራሱን በራሱ ለማስተዳደርና ለሃገሩ ሰላምና ብልጽግና መራር ትግል በማካሄድ ላይ ነው። ስለሆነም የኦሮሞ ህዝብ በወያኔ ስርዓትና በጀሌዎቹ የማስመሰያና የማታለያ ፕሮፓጋንዳና ከንቱ ጩኸት ተታልሎ ከትግሉ መዘናጋት የለበትም። የኦሮሞ ህዝብ በፊንፊኔና በመላው ኦሮሚያ ላይ ያለው የሙብት ጥያቄ ምላሽ እስከሚያገኝ ድረስ የኦሮሞ ህዝብ የነጻነት ትግል በሁሉም መስክ ይቀጥላል።

**ድል ለኦሮሞ ህዝብ!**

**የኦሮሞ ነጻነት ግንባር**

**ሚያዚያ 15, 2016**